# ረመዷን የመንፈሳውያን ቅዱስ ጊዜ እንጂ የቀድሞው ቅንጅት ስብርባሪዎች እና የደርጉ ስርአት የሳንሱር ኦፊሰሮች አይደለችም!!

**ሚስባህ**

ክፍል አንድ

የእምነት ነፃነት፣ የሃይማኖት እኩልነትና መንግስታዊ ሃይማኖት መከልከሉን የተመለከቱ ጉዳዮች ህገመንግስታዊ ዋስትና አግኝተው የየእምነቶቹ ተከታዮች ይህንኑ ነፃነት ማጣጣምና ተግባራዊ ማድረግ ከጀመሩ ዓመታት መቆጠራቸው ይታወቃል፡፡ ቀድሞም ቢሆን የመንግስታቱ ተጽእኖ እና ርዕዮተ አለም እንጂ መቻቻል መከባበሩና አንዱ ስለ አንዱ አለሁ ባይነቱ የነበረ በመሆኑ የየእምነቶቹ ተከታዮች ቀርቶባቸው የነበረው ነፃነት ህገመንስታዊ ዋስትና ሲላበስ በተግባር ለመተርጎምና ስርዓታቸውን ለመፈጸም ብዙም አልተቸገሩም፡፡ ሆኖም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የተለየ ተልዕኮአቸውን ለመወጣት የሚሹ ሃይሎች ሃይማኖትን እንደጥሩ አማራጭ እየተጠቀሙበት ነው፡፡

መጅሊስ፣ አወልያ፣ ዋልድባ እና ዝቋላ የመሳሰሉትን የቅርብ ጊዜ አጀንዳዎች ማስታወሱ ብቻ በቂ ማስረጃችን ሲሆን መንግስትና ትክክለኞቹ አማንያን ባደረጉት ጥረት የነዋልድባና ዝቋላ ጉዳዮች ቢከስሙምና የነአወልያና መጅሊሱ አጀንዳዎች ፋይላቸው ሊዘጋ ከዋዜማው ላይ ቢደረስም፣ በተለይም የአወልያ ጉዳይ መልሶ በማገርሸትና በመራገብ ላይ ስለ መገኘቱ ሰሞንኛ የሀገር ውስጥ ዘገባዎችን በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

በርግጥ የሃይማኖት ስም ያላቸውን ጋዜጦች በተመለከተ ዘገባቸው ትክክል ነው? ወይስ አይደለም? ሚዛናዊ ናቸው? ወይስ ስነ ምግባር የሌላቸው? የሚሉትን መሰረታዊ የጋዜጠኝነት መለኪያዎች እንኳ ብንተውላቸው መቼም ስማቸው ነውና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ሁሌም ማንሳታቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ ሆኖም በነፈሰበት የሚነፍሱት ጬኸትና ሁከት ልምዳቸው የሆኑት አንዳንድ የግል ጋዜጦች ደግሞ ስራቸው እንደአየሩ ስለመሆኑ ቢታወቅም ጭልጥ ብለው ይፈተፍታሉ፣ ያተራምሳሉ ብለን ግን አንጠብቅም ነበር፡፡ ምክንያቱም ደግሞ የሃይማኖት ጉዳይ የእንቁላል አይነት ጥንቃቄ ካልተደረገበት ኪሳራውና አሉታዊ ውጤቱ ጋዜጦቹን እና ጋዜጠኞቹን የሚጨምር በመሆኑ፡፡

እንደማስታወሻ ይህንን ካነሳሁኝ ዘንዳ ወደዋናው አጀንዳዬ ስመለስ የአወልያውን አገርሽቶ በተመለከተ ከግሉ ጋዜጣ የፍትህን አንድ መጣጥፍና ከሃይማኖቱ ደግሞ የሰለፊያውን ሰሞንኛ ርዕሰ አንቀጽ እና አንድ ተጨማሪ መጣጥፍ ተመልክቼ የገረመኝን፣ ያስገረመኝን እና ያሳዘኑኝን ጉዳዮች በማውሳት ምን እየተሰራ ነው? ስል ለምዕመናኑና ለሚመለከተው ሁሉ ጠይቃለሁ፡፡

ሰኔ 8 ቀን 2004 ዓ.ም በታተመችው ፍትህ ጋዜጣ ላይ ያነበብኩት መጣጥፍ “ረመዷንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ” በሚል ርዕስ ስር የሰፈረውን ነው፡፡ ፀሃፊው ሁሴን ከድር የተባሉ ግለሰብ ሲሆኑ የቀድሞ የጦቢያ መጽሄት ጋዜጠኛ የሚል ማስታወሻም ከፎቶግራፋቸው እና ስማቸው ስር ሰፍሯል፡፡

ስሜቴን ከብዕሬና ከወረቀቴ ጋር እያገናኘሁ በመፃፍ ሂደት ላይ ሳለሁ አንድ ነገር ታወሰኝ፡፡ ስለሆነም ይህንኑ ትውስታዬን  መግለጽና የመግለፄን ምክንያት መጀመሪያ ለምታነቡኝ ሁሉ መጥቀሱ ተገቢ መስሎ ተሰማኝ፡፡ ምን መሰላችሁ፦ ዛሬ በነፍትህ እና መሰል ተቃዋሚዎች ዘንድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፀረ ኢህአዴግ እና ፀረ መንግስት ናቸው የሚል የተሳሳተና የአውቆ አበድ አስተሳሰብ አለ፡፡ መንግስትን የሚያህልና ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ነው ተብሎ በነፍትህ እና ተቃዋሚዎች የሚገለጸው ገዢ ፓርቲም ሆነ ኢቴቪ እንደሚሳሳቱት ሁሉ፤ ስለተሳሳቱም እንደሚቀርብባቸው ትችት ሁሉ እነፍትህ እና ተቃዋሚዎቹም የማይሳሳቱበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ሆኖም ተሳስታችኋል ትክክል አይደላችሁም  ብለው በማስረጃ  ለሚጽፉ ግለሰቦች ሁሉ ምላሻቸው "የወያኔ ፍርፋሪ ለቃቃሚ" የሚል ይሆናል።ይህ አስተሳሰባቸው ከባህሪያቸውና ከአላማቸው የመነጨ መሆኑ ቢታወቅም በዚህ መጣጥፌ ለማውሳት የፈለግሁበት ምክንያት የምጽፈው ስለአቶ ሁሤን ከድር በመሆኑና ሁሤን ከድርም ማንነታቸው እንደሚታወቅባቸው የተረዱ በሚመስል አኳኋን ቀድሞው ስጋታቸውን እንዲህ ሲሉ በማስፈራቸው ነው፡፡

“እውነቱ ግልጥልጥ ብላ የወጣች ቀን ዛሬ ለፍርፋሪ ብለው ህሊናቸውን የሸጡ ህዝብን የማተራመስ ተንኮላቸውን በብዕር ያራመዱ ጋዜጦች አያፍሩም ይሆን? ለነገሩ ራሳቸውን በብዕር ስም ጋሻነት የከለሉ በመሆናቸው እፍረታቸው ሊታወቅ አይችልም፡፡ ብሎም የነሱ ሳይሆን የፕሮፓጋንዳው ሰለባ በመሆናቸው የታዘዙትንና ተፈልፍሎ የተሰጣቸውን አቅጣጫ ተከትለው ነው የሚሰሩት ።እስከመቼ ከህሊናቸው ተጣልተው እንደሚኖሩ ራሳቸው ይወቁት፡፡” ሲሉ በመጣጥፉቸው መጨረሻ አካባቢ አስፍረዋል፡፡ መጨረሻ አካባቢ ማስፈራቸው ደግሞ የፃፉትን ሁሉ ቀና ብለው ሲያዩት የውሸቱ መብዛት ስላሳሰባቸውና ለዚህስ ጉዳይ ወቀሳ የሚያቀርብ አይጠፋም ከሚል መነሻ የሆነ ይመስለኛል፡፡ የሆነው ሆኖ እኔ ፍርፋሪ ስለሚሰጠውም፣ የሚሰጥ ስለመሆኑም ከናንተ ሌላ ሲናገር የሰማሁት ባለመኖሩና ቢሰጥም እንኳ በብዕር ስም ተሸፍኜ የማቀርበው እንዳልሆነ እንዲህ እንደ አቶ ሁሤን ከድር በስተመጨረሻ ሳይሆን መጀመሪያ ማሳወቄ ቢያንስ አንባቢያን ሲያነቡኝ ማነው? የሚለውን ጥያቄም አብረው እየመለሱ እንዲሄዱ ያግዛቸዋልና ጥሩ ይመስለኛል፡፡

አሁን ወደ ዋናው ቁም ነገሬ ገብቻለሁ፡፡ "ረመዷንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ" ላብጠረጥረውና ልገላልጠው ነው፡፡ መጣጥፉን የምመለከተው ከሁለት ነገሮች አንፃር ነው፡፡ ከአቶ ሁሴን ከድርን እንደግለሰብ እና ከቀድሞው የጦቢያ መጽሔት ጋዜጠኛ አንፃር፡፡

አቶ ሁሤን እንደ አቶ ሁሤን ሆነው ያቀረቡትን መጣጥፍ   ይዘት ለመረዳት እንኳ ሰዋሰዋዊ ስርዓቱ የተፋለሰና የቋንቋን ህግጋት ያልተከተለ በመሆኑ ግልጽ አይደለም። ግን በግድ ይግባን፣

እንረዳው ካልን ነገርዬው የአመጽ ደወል ነው፡፡ የአመጽ ደወል ነው ብለን ከተስማማን ዘንዳ ደግሞ መላውን የእስልምና እምነት ተከታዮች ለአመጽ የሚያበቃቸው ምንድነው ?ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን፡፡ አቶ ሁሤን ከድር እስልምና ስለተደፈረ መንግስት ስላርመጠመጠው እጁን ያወጣ ዘንድ አመጽ ሊያውም በረመዱን ብቸኛው አማራጭ ነው ሲሉ ይከራከሩና ስለ እስልምና እምነት መበደል የሚያቀርቡት አስረጅ ግን ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል አይነት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ታድያ ምን እያሉ ነው? ብለን ስለ አቶ ሁሤን ከድር ማሰላሰላችን መቼም የግድ ነው፡፡ አሰላስለን ስናበቃ የምንደርሰው ደግሞ ከሁለተኛው  ማንፀሪያዬ ላይ ይሆናል፡፡ ወይም የቀድሞ የጦቢያ መጽሄት ጋዜጠኛ የሚለው ማንጠርጠሪያዬ ላይ፡፡

አሁንም አቶ ሱሴን ከድር እና "ረመዱንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ" የሚለው መጣጥፋቸው ላይ ነኝ፡፡ በግድ ወደገባን የመጣጥፋቸው ይዘት እንግባና ክሳቸውን ከማስረጃዎቻቸው ጋር እያይዘን እንመርምረው፡፡

“መስጂድ የፀሎት ስፍራ  ብቻ አይደለም የእስልምና ሃይማኖታዊ እውቀቶች 80 በመቶ የሚሰጡት መስጅድ ውስጥ ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ መስጅድ የእውቀት ማዕከል፣ የሥነ ምግባር ማነጪያ ስፍራ፣ የትውልድ ማፍሪያ፣ የመንፈሳዊ እምነት ማጎልበቻ፣ የአለማዊ ህይወት ስርዓት ማነጫም ነው፡፡ ከህልፈተ ህይወት በኋላ የሚች ፍትሃተ ፀሎት ማከናወኛም ስፍራ ነው፡፡ ማንኛውም ሙስሊም ሚች በመስጅድ ሳይሰገድበት ወደመቃብሩ አይወሰድም፡፡” ይህን የሚሉት አቶ ሁሴን ከድር ናቸው፡፡ ነገር ግን አቶ ሁሴን ከድር ብቻ ሳይሆኑ ከላይ ስለመስጅድ በተገለጸው ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ መላው አማንያን በሚገባ እንደምንስማማ እርግጠኛ ሆኜ መናገር እችላለሁ፡፡ ሆኖም ከላይ እንደመወስወሻ አይነት ነገር ስለመስጅድ ውክልና የደረደሩልን አቶ ሁሴን ቀጥለው ያመጡት ሃሳብ ግን ለምዱን የተከናነበው ተኩላውን አይነት ነው። ምን አሉ መሰላችሁ፡፡

“በነቢዩ መሃመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን መስጅድ የጦርነት እቅድ መንደፊያ ስፍራ፣ የሀገር ጉዳይ መወያያ አዳራሽ (ዛሬ ፓርላማ እንደምንለው) ሁሉ ነበር፡፡” እንደወረደ ሲታይ እውነት ይመስለናል፡፡ ነገር ግን በነብዩ መሃመድ ዘመን በመስጅድ የሚታቀደው ጦርነት ምን አይነት ጦርነት ነው? ሀገራዊ ጉዳይ ሲባልስ ምን ማለት ነው? ፖለቲካ ማለት ነው? ህገመንግስታዊ ስርዓትን መናድና መፈንቅለ መንግስት መጠንሰስ ማለት ነው? አመጽና ሁከት ማለት ነው? የነብዩ መሃመድ ዘመን መስጅድና አማንያን እንዲሁም መንግስታዊ ስርዓቱ ምን ነበር? አሁን ካለንበት ዘመንና መስጅዶቻችን ፣መንግስታዊ ስርዓቱና ህገመግስታችን ስለእምነታችን ምን ይላሉ? በአቶ ሁሴን በደንብ አልተዘረዘረም፡፡ ያልተዘረዘረው ደግሞ "ላም ባልዋለበት….." አይነት ምዕመኑን ለማሰለፍ ስለተፈለገ እንጂ ስለነብዩ መሃመድ ዘመን የተገለጸው ሁሉ አሁን በአወልያው በኩል ከተነሳው አጀንዳ ጋር ምንም አይነት የጊዜ የሁኔታና የምክንያት ግንኙነት የላቸውም፡፡

አሁንም አቶ ሁሴን ከደር አንደ አቶ ሁሴን ቀጥለዋል “. . . ከሰሞኑ ሙስሊሙ ህብረተሰብ መሪዎቹን የመምረጥ መብት ይኑረኝ በሚል ያቀረበውን ጥያቄ መንግስት መሪዎቹን ሊመርጥለት ሽቶ እንደሆነ ባይታወቅም በይፋ በማይታወቅበት መልኩ በጓሮ በር በወረዳ ደረጃ አንዳንድ ሰዎች እየተጠሩ የምርጫ ድራማ እየተለማመዱ ነው የሚባል ወሬ፣ እየተሰማ ነው፡፡ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ባላረጋግጥም” አቶ ሁሴን እዚህ ላይ መጀመሪያ እውነት መሆኑን ያላረጋገጡት ጉዳይ ላይ መፃፍዎ ምን ያህል እንዳቀለለዎና ይህም በተጨባጭ በራስዎ ላይ እንደመሰከሩ የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ የመጣጥፉም አላማ የበለጠ ግልጽ የሆነበት አንቀጽ ነው፡፡

በመቀጠል ግን በወረዳ ደረጃ ምናምን የሚሉት ቀደም ብለው ከመጣጥፉ መግቢያ አካባቢ ስለመስጅድ አገልግሎት በገለጹበት አርፍተነገር ውስጥ ስጋትዎን የሚያመላክት ነገር ጠቆም ስላደረጉን ፣ማለትም መስጅድ የምርጫ ቦታ መሆኑን ስላወሱን፣ በወረዳ ደረጃ የሚካሄደውን ምርጫ እያጥላሉትና እየተዘባበቱበት እንደሆነ እንደምንም የተዛባውንና የተፋለሰውን የሰዋሰው ስርዓት ገጣጥሜ ተረድቼዎታለሁ፡፡

በዚህ ከተግባባን በነብዩ መሃመድ ዘመን የነበሩትን የእስልምና እምነት ተከታዮች ብዛትና ሌሎች ማህበረ አኮኖሚያዊ ጉዳዮች ለማስታወስ ከፈቀድን ምርጫው በወረዳ ደረጃ መካሄዱን ባልነቀፍም፣ አሁን ከ30 ሚሊዮን በላይ እንደሆነ የሚገለጸው አማኒ በየትኞቹ መስኪዶች ተገኝቶ ምርጫ ማከናወን ይችላል? ብለን መጠየቅ ግድ ይለናል፡፡ ምርጫው የሃይማኖት መሪዎቻችንን የምንመርጥበት የሚወክሉንን ይፋ የምናደርግበት እንጂ የአወልያውን ኮሚቴና መጅሊሱን የምናረካክብበት እንዳልሆነ አቶ ሁሴን እስከተስማሙ ድረስ በመላው ሙስሊም ስም መጅሊሱንና መንግስትን ሲሞግቱ የከረሙት አቶ ሁሴንና መሰሎቻቸው ምርጫው ቲፎዞዎቻቸው በተሰገሰጉበት መስጂዶች ብቻ ይሁን ብለው ባልተከራከሩ ነበር፡፡ ሆኖም መነሻው ሌላ ነው ሲባል የነበረውን የመንግስት ክስ እነ አቶ ሁሴን ተደራሽነት የሚኖረውን በወረዳ ደረጃ የሚካሄድ ምርጫ በመቃወም እያረጋገጡልን ነው፡፡

ሌላው የአቶ ሁሴን መከራከሪያ የዘቀጠ መሆኑን የሚያመላክተን ደግሞ በእኛ ዘመን በተለይም የእምነት ነፃነት ህገመንግስታዊ ዋስትና ካገኘ በኋላ መቼ ነው በመስጅድ ደረጃ ምርጫ ተካሂዶ የሚያውቀው? ብለው ለመጠየቅ አለመሞከራቸው ምናልባትም እሳቸው የጠረጠሯቸውን ባለብእር ስሞች ሆነውት ተገኝተው እንዳይሆን ፣በሌላ አነጋገር ከእምነቱ ውጪ ያሉ አላዋቂ ሳሚ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ጥርጣሬን አጭሮብኛል፡፡

አሁንም ከአቶ ሁሴን ብእር እና "ረመዷንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ" መጣጥፋቸው ጋር ነኝ፡፡ “መንግስት በሙስሊሞች መቼ ተለወጠ?” ሲሉ በንዑስ ርዕስ የሚጠይቁት አቶ ሁሴን ዊክሊክስን እንደማጣቀሻ በመጠቀም ለራሳቸው ጥያቄ ያቀረቡት ምላሽ የግለሰቡን ተልካሻነት የበለጠ ያጎላና ጥርጣሬዬን ወደ እውነታነት ለመቀየር የ50 በመቶ ድርሻ ያለው አጀንዳ ሆኖብኛል ፡፡

ወሃቢዝም በኢትዮጵያ ማቆጥቆጥ የጀመረው ከአሜሪካ መንትያ ህንፃዎች የሽብር ጥቃት በኋላ ነው፤ ከዛ በፊት ያልነበረ ጭራቅ ነው፤   ብሎ ዊክሊክስ ይፋ ቢያደርግም መረጃውን ከየት እንዳመጣው አላውቅም ሲሉ ዊክሊክሰን የሚያጣጥሉት አቶ ሁሴን ወሃቢዝም/አክራሪነት/ ቀድሞ የነበረ መሆኑንም እግረ መንገዳቸውን መስክረዋል፡፡ ቢያንስ እሳቸው ወሃቢያ መሆናቸው ላይ እርግጠኛ ስለሆኑም ይመስለኛል ደፍረው ዊክሊክስን ያናናቁት፡፡ በሌላ በኩል የዊክሊክስን ውሸታምነትም ማረጋገጣቸው ይመስለኛል "ከየት እንዳመጣው አላውቅም" ማለታቸው ።ግን ዊክሊክስ ውሸታም ነው ብለው ለመዝለቅ ከአላማቸው ጋር ሊያላትማቸው ሆነባቸው እና ብዙም ዝቅ ሳይሉና ለሌላ ቀን እንኳ ሳያሳድሩ የዊክሊክስን መረጃ ማንቀለጳጰስና የአመጽ ጥሪያቸው ማጣፈጪያ ቅመም ማድረግ ጀመሩ፡፡ ላይና ታች በመርገጥ መዘባረቅ ታዲያ ይህ አይደለም?

አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ይስፋፋል ብላ የምታስበውን አክራሪነት ለመግታት ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ የእቅድ ለውጥ ማድረጓን ከዊክሊክስ አገኘሁት የሚሉን አቶ ሁሴን ከነዚህ ለውጦች መካከል አክራሪነትን በምትጠረጠርባቸው ሀገራት የኢኮኖሚ ድጋፍ ማድረግ፤ ከእስልምና አስተምህሮ ይልቅ እስልምናን ወደባህላዊ እምነት የመለወጥ የአልህበሽን አስተሳሰብ ማስረጽ፣ የእስልምና አጋርነቷን ለማሳየት ደግሞ የመስጂዶች እድሳት ማድረግ የሚሉቱን የዘረዘሩልን አቶ ሁሴን፤የዊክሊክስ ሌላው መረጃ በማለት ደግሞ ተከታዩን ይገልጻሉ "የወሃብያ ተጽእኖን ለመቋቋም ባህላዊ መርሃግብሮችን ማከናወን በሚል ርዕስ ኤምባሲው ወደ አሜሪካ የላከውን ትንታኔ የሚያጋልጥ ነው"፡፡ ኤምባሲው ከላይ እንደገለጽኩት እስልምናን ለማሸመድመድ ከተፈለገ ባህላዊ እሳቤዎችን ማጠንከር ነው፡፡ ለዚህም ለቦታዎች ለቁሳቁሶች ለልማዳዊ ተግባራት ትኩረት ሰጥቶ በመስራት የሰዎችን የትኩረት አቅጣጫ ማሳትና የትርኪ ምርኪ አስተሳሰብ ማጠራቀሚያ ማድረግ ነው፡፡" ሌላም ሌላም ዘርዝረዋል፡፡

በዚህ የዊክሊስ መረጃና የአቶ ሁሴን እሳቤ መሰረት ወሃቢዝምና ሱፊ የተለያዩ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንችላለን፡፡ ታዲያ ይህ ከሆነ ከዚህ የዊክሊክስ መረጃ ቀደም ብለው አቶ ሁሴን "መንግስት ለክፉ የተመኘው ህዝበ ሙስሊም በተቃራኒው በፍቅርና በወዳጅነት መንፈስ በመሰባሰብ አንድ መሆን ጀምሯል" ማለታቸውን ምነው ዘነጉትሳ፡፡

ወደሌላው ከዊክሊክስ ጋር ወደተያየዘው የአቶ ሁሴን ገለጻ ስናልፍ ደግሞ ሰውዬውና መሰሎቻቸው የቀድሞው ቅንጅት ስብርባሪ ቱልቱላዎች ስለመሆናቸው እንገነዘባለን፡፡

ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ካለችው የኢኮኖሚ እድገትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አንፃር በቀጣናው የበላይ መሆኗን በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ማረጋገጥ ከጀመረች ሰንብታለች፡፡ የአለም አካል የሆነችውና ከሃገራቱ ሁሉ የዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ማማ ነች የምትባለዋ አሜሪካ ከየሀገራቱ ጋር ከሚኖራት የልማትና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ ወሃቢዝም

ቢስፋፋ አሜሪካ ብዙ አጀንዳዎች የዘረጋችበት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የረብሻ እንደሚሆን በመገንዘብ በአክራሪዎቹ የተጠቃውን ለዘብተኛ የሱፊ ክፍል የመርዳት እቅድ ማስቀመጧ የሚጠበቅ ጂኦ ፖለቲካል ስትራቴጂ እንጂ አዲስ ነገር እና የሚገርም አይደለም፡፡

ያም ሆኖ አሜሪካ እነ አቶ ሁሴንና መሰል የአወሊያ ቡድኖችን ልታጠፋ ነው አይነት ወሬ በዊክሊክስ አስረጂነት ያቀረቡት ሃሳብ ተጠየቃዊ ሳይሆን በምርጫ 97 ወቅት የነበረው ቅንጅት የሚከተለውን አይነት አሳቻ አካሄድ ነው የሆነብኝ፡፡ ምክያቱም የቀድሞው ቅንጅት አጀንዳ በማሳት ለእሱ ከተስማማ እንኳን የአሜሪካንን የሰይጣኑንም መረጃ ይኸው ብሎ ለመከራከሪያ ሲያቀርበው እንደነበረው ሁሉ አቶ ሁሴንም ለእሳቸውና ለመሰሎቻቸው የማይስማማውን የዊክሊክስ መረጃ ከየት አባቱ እንዳመጣው አላውቅም አይነት ማጣጣያ ያቀርቡና ከነእርሱ አላማ ጋር ሰምሮ ያገኙትን ደግሞ የዊክሊክስ መረጃ እንደሚያመለክተው ሲሉ ከመቀመቅ የወረወሩትን ሰይጣኑን ዊክሊክስ መልሰው በማጥመቅ ፃድቅ አድርገውት ወዲያውኑ ወደ ገነት መግቢያ በር ያደርሱታል፡፡

ይህም ይሁን፤ ዊክሊክስ መቼም ለእነ አቶ ሁሴን ብቻ በራዕይ የተገለጸ መረጃ አይደለም፤ እኛም ሁሉም ማየት የፈለገ ሁሉ ጎግሉን መጎልጎል ብቻ ነው የሚጠበቅበት፡፡ ከዚያስ? እስልምናን በተመለከተ አቶ ሁሴን ያሰፈሩልንን መረጃ ብቻ ሳይሆን የምናገኘው አሜሪካ ለለዘብተኛው ሡፊና በአቶ ሁሴን ለተገለጹት መስጂዶች ድጋፍ ለማድረግ የፈቀደችበትን ማብራሪያም እናገኛለን፡፡

አወልያውና አቶ ሁሴን የሚሞግቱለት አክራሪ ብድን በኢትዮጵያ የሱፊ ሱኒ መንፈሳዊ ማእካላዊ ተቋማትን ሆን ብሎ ለማጥፋት መንቀሳቀሱን የሚገልጸው ዊክሊክስ ጀማ ንጉስ በወሎ፣ አሳጃና መስጂድ ባሌና አርሲ፣ ድሬ ሼህ ሁሴን፣ ሃረር የአባድር ሳይቶች ሁሉ የዚህ ቡድን የጥቃት ኢላማዎች እንደነበሩና እነዚህ አክራሪዎች በርካታ መስጅዶችን እንዳቃጠሉ፣ የመቃብር ቦታዊችን እንደፈነቀሉና በርካታ ወንጀሎችን እንደፈጸሙ መረጃው ያትታል፡፡ አቶ ሁሴን ታዲያ ለምን ይህን መረጃ አያይዘው አልገለጹም፡፡ በእሳቸው እምነት ወሃቢዝምና የሱፊው ሱኒ አንድ ስለሆኑ ማን ማንን ያጠፋል ለማለት ነው ፡፡ “ለማያውቅሽ ታጠኚ” ስብርባሪ ስለመሆናችሁ ደረስንበት። አቶ ሁሴን እንደ አቶ ሁሴን "ረመዷንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ" ከሚለው መጣጥፋቸው ጋር እዚህ ድረስ ተፈተሹ፡፡ እዚህ ላይ እንረፍና በ2ኛው ክፍል ስንመለስ አቶ ሁሴን ከድርን እንደ ቀድሞው የጦቢያ መጽሄት ጋዜጠኛ "ረመዷንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ" ከሚለው መጣጥፋቸው ጋር እንፈትሻቸዋለን፡፡ እናሰላስላቸዋለን፤ በርግጠኛነትም የቀድሞው ቅንጅት ስብርባሪ የደርጉ ስርአት የሳንሱር ኦፊሰር የመሆናቸው እውነታ ላይ እንደርስበታለን፡፡